# ፈጣን ማጣቀሻ፣ Personal Care Aide Services (PCA)

ብዙ ጉድለት ያለባቸው በእድሜ የገፉ እና አዋቂዎች በተለመደ አካባቢ መቆየት እና የጤና አገልግሎቶች እና የረጅም ጊዜ እንክብካቤ በቤታቸው ወይም በማህበረሰባቸው ውስጥ ማግኘትን ይመርጣሉ። በግዛቱ ያሉ ብቁ የሆኑ በእድሜ የገፉ እና ጉድለት ያለባቸው ግለሰቦች በግለሰብ መኖርያ ቤት ወይም በማህበረሰብ ስፍራ ለሚሰጥ የእለት ተእለት የአኗኗር እንቅስቃሴ ድጋፍ፣ Personal Care Aide Services(PCA) ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በግዛቱ የElderly and Persons with Physical Disabilties(EPD) ነጻ መርሀግብር ውስጥ የተመዘገቡ ግለሰቦች የPCA አገልግሎቶች ለማግኘት ብቁ ናቸው፣እና የEPD ነጻ መርሀግብር መስፈርቶች የማያሟሉ ሌሎች ግለሰቦችም ቢሆን በግዛቱ የመንግስት የግል እንክብካቤ መርሀግብር እቅድ አማካኝነት ለPCA ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ከታች የተገለጸውን መስፈርት እንደሚያሟሉ ካሰቡ(ወይም ምዘናውን አስቀድመው ሞልተው ለPCA ብቁ መሆንዎን የሚያውቁ ከሆነ)፣ከታች ባለው ቁጥር Aging and Disability Resource Center(ADRC)ን ያግኙ።

**የPCA አገልግሎቶች ለእርስዎ ትክክለኛ የሆነ የተለያዩ ማእቀፍ ያላቸው ድጋፎች እና አገልግሎቶች ያቀርባሉ።**
የግል እንክብካቤ ረዳቶች ሰፊ ማእቀፍ ያላቸውን መደበኛ እንቅስቃሴዎችን ያከናውናሉ፣የሚያካትተው፣

- ምልክት መስጠት ወይም መሰረታዊ በሆኑ የግል እንክብካቤ ላይ እርዳታ መስጠት፣የሚያካትተው ገላ ማጠብ፣ማልበስ፣እና ሽንት ቤት ወይም የአልጋ ላይ መጸዳጃ
- የመቆጣጠር እንክብካቤ እርዳታ፣የሚያካትተው ካቲተር መቀየር ostomy(ኦስቶማይ)አቅርቦቶች ወይም ተከላካይ የውስጥልብሶች
- በታዘዘው መሰረት ከዝውውር፣መመላለስ፣እና እንቅስቃሴዎች ጋር እርዳታ
- አስፈላጊ ምልክቶችን ማንበብ እና መረዳት እንደ የሰውነት ሙቀት፣ የልብ ምት እና የመተንፈስ መጠን
- በአካል ሁኔታ፣ጸባይ ወይም እይታ ላይ ያሉትን ለውጦች መመልከት እና መከታተል
- ምግብ ማዘጋጀት እና እንዲመገቡ መርዳት
- ኢንፌክሽን መቆጣጠር
- ጤናን፣ደህንነትን እና ምቾትን ለመጠበቅ እንዲቻል የሚኖሩበትን አካባቢ መጠበቅ ላይ እርዳታ
- የህክምና ቀጠሮዎችን፣የስራ ቦታ፣ ወይም የተፈቀዱ እንቅስቃሴዎች ጋር አብሮ መሄድ
- የተመጣጠነ ምግብ ወይም ሌላ ጤና ጋር የተያያዙ እቃዎችን አብሮ መግዛት
- ስልክ አጠቃቀምን መርዳት
- መድሀኒት እራስ-መጠቀምን መርዳት(PCA ለግለሰብ መድሀኒት በቀጥታ አይሰጥም)

**የPCA አገልግሎቶችን ለመጠቀም ብቁ ለመሆን፣ እርስዎ መሆን አለብዎ**

- ለግዛቱ የEPD ነጻ መርሀግብር ብቁ መሆን እና መመዝገብ፣ ***ወይም***
- በግዛቱ የመንግስት የPCA እቅድ መርሀግብር ለመመዝገብ የሚያስፈልጉትን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት፣
    - የColumbia ግዛት ነዋሪ መሆን
    - የU.S. ዜጋ መሆን ወይም ህጋዊ የስደተኛ ሁኔታ መያዝ
    - የDC Medicaid ለመቀበል ብቁ መሆን፣ ከ100%FPL ያነሰ ገቢ ያለው
    - በየእለትለት ኑሮ እንቅስቃሴ እርዳታ መፈለግ እና ለPCA አገልግሎቶች የተቋቋመውን የ"እንክብካቤ ደረጃ" ማሟላት

**የPCA አገልግሎቶች ለእርስዎ ትክክለኛ ናቸው?** የPCA አገልግሎቶች፣ እንደ ሁሉም ቤትን እና ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ የረጅም ጊዜ የMedicaid አገልግሎቶች እና እርዳታዎች፣ የምርጫ መርሀግብር ናቸው።ለመሳተፍ ወይም ላለመሳተፍ እና የአገልግሎቶችዎን አቅራቢ የመምረጥ መብት አሎት። ከላይ የተገለጹት አገልግሎቶች የእርስዎን ፍላጎቶች እንደሚያሟሉ ካሰቡ PCA ለእርስዎ ጥሩ ምርጫ ሊሆን ይችላል።

**የቤት ውስጥ ጉብኝት እና ምዘና አስቀድመው ሞልተዋል? ከምዘናዎ በኋላ በደረሶት ደብዳቤ ላይ የምዘና ውጤትዎን ይመልከቱ።**
የተለጠፈው አጠቃላይ የምዘና ነጥብ <u>9 ወይም ከፍተኛ ከሆነ፣</u> ለነጻ መብቱ መስፈርት የሆነውን የተግባር ብቃት አሟልተዋል እና በነጻ መብቱ አማካኝነት PCAን ማግኘት ይችላሉ። ከመድሀኒት መጠቀም ውጪ የተለጠፈው የተግባር ምዘና ነጥብዎ <u>በ 4 እና 8 መካከል</u> ከሆነ፣በMedicaid የመንግስት እቅድ ስር የPCA የተግባር መስፈርትን ያሟላሉ፣እና በመርሀግብሩ ውስጥ ሌላውን መስፈርት ካሟሉ በዚያ መርሀግብር ሊመዘገቡ ይችላሉ።

**ለበለጠ መረጃ፣የእርሶን አማራጮች ለመረዳት፣ወይም በPCA እንዴት መመዝገብ እንደሚችሉ ለመረዳት** የAging and Disability Resource Center(ADRC) በ 202-724-5626 ወይም በኢሜይል Ask.ADRC@dc.gov ያግኙ። በተጨማሪ ወደ Department of Health Care Finance(DHCF) Long Term Care Administration ጋር በ202-442-5988 መደወል ይችላሉ።